የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/0202/13

ቀን/Date ሰዳር 0 4 2013

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

የኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/70 ቀን 01/03/2013 በተጻፈ ደብዳቤ ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀፅ 43 መሸጋገሪያ ድንጋጌ ጋር በተያያዘ ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ የሚስተናገዱ ተመላሽ ኢትዮጵያዊያን ወደ ሀገር የሚያስገቧቸው ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ አዋጁ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ተጭነው በአዋጁ መሸጋገሪያ ጊዜ ውስጥ ወደ ሀገር የገቡ እንዲሁም አዋጁ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ወይም በኋላ ተጭነው ከአዋጁ መሸጋገሪያ ጊዜ በኋላ በተመላሽ ኢትዮጵዊያን ወደ ሀገር የገቡ ተሽከርካሪዎች የሚስተናገዱበትን አግባብ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ከኮሚሽኑ በተጠየቀው መሠረት፡-

1. የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ከፀናበት ቀን በፊት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮቫሉታ) ታዘው አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች በሚኒስትሮች ም/ቤት የፍራንኮቫሉታ ደንብ የተፈቀዱ እስከሆኑ ድረስ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበሰበው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 (እንደተሻሻለ) መሠረት ስለመሆኑ ቀደም ብሎ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ መጋቢት 25 ቀን 2012 በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/360 በተገለጸው አግባብ መሆኑን፤

2. ውጭ ሀገር ሲኖሩ የነበሩና ጠቅልለው ወደ ሀገራቸው ስለመመለሳቸው ከሚኖሩበት ሀገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንጽላ ጽ/ቤት አዋጁ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የድጋፍ ደብዳቤ የተጻፈላቸው ሆኖ አዋጁ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ አንስቶ በ6 (ስድስት) ወር ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪን ጨምሮ የግል መገልገያ ዕቃዎቻቸውን አስጭነው በፍራንኮቫሉታ ፈቃድ ያስመጡ ተመላሽ ኢትዮጵያዊያን ብቻ በተራ ቁጥር 1 በተገለጸው መሠረት ማስተናገዱ ተገቢ ስለመሆኑ የታመነበት መሆኑን በመግለጽ አዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በ6 (ስድስት) ወር ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪዎቻቸውን አስጭነው በፍራንኮቫሉታ ፈቃድ ወደ ሀገር ያስገቡ ተመላሽ ኢትዮጵያዊያን በአዋጁ አንቀፅ 43(3) መሠረት እንዲስተናገዱ አሳውቋል፡፡

በመሆኑም በገንዘብ ሚኒስቴር ውሳኔ መሠረት ተፈጻሚ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማብራሪያ የሰጠበትን 01 ገጽ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደር እንዲሰፍን ተግተን እንሰራለን !

ስልክ/Tel:- +251 116 62 98 00
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: customscommission@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>፡

ጉ/ክ 13ፅ0
01/03/2013

25

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No ታ/ክ/ቀ/5/770
ቀን
Date 01/03/2013

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀጽ 43 መሸጋገሪያ ድንጋጌ ጋር በተያያዘ ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ የሚስተናገዱ ተመላሽ ኢትዮጵያውያን ወደአገር የሚያስገቧቸው ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ መ/ቤታችን ግንቦት 26 ቀን 2012 ዓ.ም. በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/370 በተፃፈ ደብዳቤ በሰጠው ማብራሪያ መሠረት የተስተናገደ መሆኑን አስታውሳችሁ አዋጁ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ተጭነው በአዋጁ መሸጋገሪያ ጊዜ ውስጥ ወደአገር የገቡ እንዲሁም አዋጁ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ወይም በኋላ ተጭነው ከአዋጁ መሸጋገሪያ ጊዜ በኋላ ወደአገር በተመላሽ ኢትዮጵያውያን የገቡ ተሽከርካሪዎች የሚስተናገዱበትን አግባብ በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጣችሁ ጥቅምት 11 ቀን 2013 በቁጥር 4/0106/13 እንዲሁም ግንቦት 19 ቀን 2012 በቁጥር 4/0845/12 በተፃፉ ደብዳቤዎች የጠየቃችሁትን ይመለከታል፡፡

1. የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ከፀናበት ቀን በፊት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮ ቫሉታ) ታዘው አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች በሚኒስትሮች ም/ቤት የፍራንኮ ቫሉታ ደንብ የተፈቀዱ እስከሆኑ ድረስ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበሰበው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 (እንደተሻሻለ) መሠረት እንደሆነ ከዚህ በፊት በመ/ቤታችን መጋቢት 25 ቀን 2012 በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/360 በተፃፈ ደብዳቤ በተሰጠው ማብራሪያ የተገለፀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

2. ውጭ አገር ሲኖሩ የነበሩና ጠቅልለው ወደ አገራቸው ስለመመለሳቸው ከሚኖሩበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንጽላ ጽ/ቤት አዋጁ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የድጋፍ ደብዳቤ የተፃፈላቸው ሆኖ አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ አንስቶ በ6 (ስድስት) ወር ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪን ጨምሮ የግል መገልገያ ዕቃዎቻቸውን አስጭነው በፍራንኮ ቫሉታ ፈቃድ ያስመጡ ተመላሽ ኢትዮጵያውያንን ብቻ በተራ ቁጥር 1 በተገለፀው መሠረት ማስተናገዱ ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ስለዚህ አዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በ6 (ስድስት) ወር ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪዎቻቸውን አስጭነው በፍራንኮ ቫሉታ ፈቃድ ወደአገር ያስገቡ ተመላሽ ኢትዮጵያውያን በአዋጁ አንቀጽ 43(3) መሠረት እንዲስተናገዱ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

[signature] ... ተካልኝ (ዶ/ር)
...ር ዴኤታ

ግልባጭ፣
ለኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ
<u>አዲስ አበባ</u>

ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter Hab/GT

ስልክ Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98 / 251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia